## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የጸሎት አርዕስት

በፊታችን ላለው የሽማግሌዎች ምርጫ እየጸለይን እንድንቆይ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በDecember 10 and 17 ጥቆማ ይደረጋል በDecember 24 ምርጫው ይፈጸማል።

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ በገባችሁት ቃል መሰረት የፈጸማችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ስጦታውን እስከ አመቱ መጨረሻ (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች።

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም በመገኘት አብረን እንድንጸልይ እና ቃሉን እንድንማር እናበረታታችኋለን። በወንድማችን ሲሳይ የተጀመረውም "ጸጋ" የተሰኘው ትምህርት እንደቀጠለ ነው። ጸሎት ለሚሹም እንጸልያለን። ሁላችንም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንሁን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የቺካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




## "...አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ።"

(2ጢሞ. 2:1)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**November 26, 2017**

**ሕዳር 17፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| አምልኮ........................ | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም አያሌው አስፋው |
| ቃል ............................ | ወንድም ጌቱ ጳውሎስ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

**<u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>**

"አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጸችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።"
(ሐዋ. 20፡32)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኀ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**ጸሎት አስተምረን -- የኃጢያት ይቅርታ (ክፍል አስራ-ሁለት)**

*"እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ ጌታ ሆይ... እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፦ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... <u>ኃጢአታችንንም ይቅር በለን</u>..." (ሉቃ. 11፡3)*

በአባታችን ሆይ ጸሎት ውስጥ ሌላው የምንጸልየው ሃሳብ ስለ ኃጢያት ይቅርታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ስለነበርንበት ሁኔታ ሲያነሳ በኃጢያታችንና በበደላችን ሞታን እንደነበርን ይናገራል። (ኤፌ. 2፡1) የምንመላለሰው የዲያቢሎስን ፍቃድ በማድረግ ነበር። የስጋችንንም ምኞት እየፈጸምን እንኖር ነበር። ከፍጥረታችንም ለእግዚአብሔር ቁጣ የተጠበቅን የቁጣ ልጆች ነበርን። አሁን ግን ሙታን ለነበርነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወት ተሰጥቶናል። ከኃጢያት ባርነት ወጥተን ለእግዚአብሔር ፍቃድ የምኖርበትን የጸጋ አቅም አግኝተናል። ከቁጣ ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት መጥተናል። ይህ ሁሉ የሆነልን ከእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅርና ምህረት የተነሳ ነው። እኛ ይቅር የተባልን፣ በምሕረት ኩነኔ የቀረልን ሰዎች ነን። እንግዲህ በእግዚአብሔር ጸጋ የማይገባንን የኃጢያት ይቅርታ አግኝተናል።

እለት እለት ስንኖር ደግሞ ለመተላለፋችን የሚሆን የኃጢያት ይቅርታ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንቀበላለን። በ1ኛ ዮሐንስ ላይ እንደምናነበው ኃጢያታችንን ብንናዘዝ እግዚአብሔር "ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።" (1፡9) የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም አንጽቶ ቀድሶናል። አሁንም ደግሞ በክርስትና ህይወት ስንመላለስ ለመተላለፋችን መንጻት የክርስቶስ ኢየሱስ ደም አለን። ክርስቲያን በሐጢያት ጸንቶ ሊኖር አይችልም ነገር ግን በክርስትና ሕይወት መተላለፍ ሊኖር ይችላል። ድካም ሊኖር ይችላል። ያን ጊዜ ስለ ኃጢያት ይቅርታ መጸለይ አስፈላጊ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሚያመለክተን ድካማችን ሁሉ ላይ ድምጹን እየሰማን በንስሃ መቅረብ ትክክለኛ የክርስትና አቋም ነው። ድካምን መካድ መፍትሄ አይሆንም ነገር ግን በድካማችን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ መታደስንና ጸጋን እንድናገኝ ያደርገናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ ድካም የሚራራ ሊቀ ካህናችን ነው። "ጌታ ሆይ ይህንን መተላለፌን፣ ይህንን ድካሜን ይቅር በለኝ" ስንለው ስለኛ ሆኖ እንደ ታረደ በግ ከሚታየው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሳ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል። ምህረትን ያደርግልናል።

ወገኖቼ፦ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ዳግም እድልን የሚሰጥ አምላክ ነው። ልጆቹን እስከ መጨረሻው ወዷል። የጠፋው ልጅ ወደ ቤት በተመለሰ ጊዜ አባቱ ከሩቅ አይቶት ወደ እርሱ ሮጦ አቀፈው፤ ልብሱ እንዲለወጥለት አደረገ፤ ቀለበት አደረገለት። ድግስ፣ ምስጋናና ደስታ ሆነ። እምላካችን የምህረት አምላክ ነው! በልጆቹ ንስሃና መመለስ ደስ ይለዋል። እናስታውስ የእግዚአብሔር ዙፋን የጸጋና የምሕረት ዙፋን ነው። አሜን!